መዝሙረ ተዋሕዶ

"ለከ እሠውእ መሥዋእተ ሰብሐት ፡ ለአንተ የምሰጋና መሥዋዕትን እሠዋለሁ"

መዝ. ፩፻፲፮ (፩፻፲፮)፡፫

አዘጋጅ

በኢተዋህቤክርስቲያን ሰትቤማመምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን ደሴ ማዕከል

ምዕራፍ አንድ

የመዝሙር
ምንነትና አጀማመር

፰. ፰ የመዝሙር ምንባቦች

መዝሙር፡- ዘመረ አመሰገነ

- ምስጋና ማለት ነው፡፡
- ስልት ባለውና ልብን በሚመስጥ ቃና ተቀነባብሮ ከጉሮሮ የሚወጣ ድምፅ ነው፡፡
- ልዑል እግዚአብሔር የሚመሰገንበት፣ የሚቀደስበት፣ የሚለመንበት ዐቢይ የጸሎት ክፍል የሆነ ጣዕመ ዜማ ነው፡፡
- መዝሙር ለእግዚአብሔር የሚቀርብ መስዋዕት ነው፡፡ "ለከ እሠውእ መሥዋዕተ ስብሐት" መዝ. ፩፻፲፮ (፩፻፲፭)፡፫

ዕብ ፲፫፡ ፲፭

፭. ፪ የመዘመር ዓይነቶችና ጥቅማቸው

፩. የምስጋና መዝሙር፡-

- እግዚአብሔርንና ቅዱሳኑን *በተመሰጠ* ለማመስገን ይጠቅማል፡፡ ምሳሌ ስብሐት ለአምላክነ ወመድሐኒነ

፪. የንስሐ ፣የልመና፣ የይቅርታ መዝሙር፡-

- ልመናን ለማቅረብ (ለጸሎት) ይጠቅማል፡፡
- ምሳሌ እንደ ቸርነትህ አቤቱ ማረን

፫. ትምህርታዊ/ትምህርት ሰጭ/ መዝሙር፡-

- ለመማርና ለማስተማር

ሀ. ዶግማ፡- ፲፭፡፪

ለ. ቀኖና፡- መዝ. ፩፻፶፡፶፬

ሐ. ትውፊት፡- መዝ. ፩፻፴፩ ፡፲፪፣ ዘዳግ. ፴፪፡ ፩ - ፵ ፷

የቀጠለ...

ከዚህም በተጨማሪ መዝሙር

- ክፉ መንፈስን ያርቃል፤ ፩ኛ ሳሙ ፲፮ ፡ ፳ ፫
- አጥንትን ያለመልማል፤ ቅዳሴ ማርያም።

፩. ፫ የመዝሙር አጀማመር

፩. መዝሙር በዓለመ መላእክት

- በሳጥናኤል ክህደት ባልተናወጡ ቅዱሳን መላእክት ተጀመረ።
- የመላእክት ተፈጥሮ ለምስጋና ነውና። ኢሳ. ፮፡ ፫
- በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ ይዘምራሉ።

፪. መዝሙር በሰው ልጆች ዘንድ

- ሰውና መላእክት የተፈጠሩት ስሙን ለመቀደስ፣ ክብሩን ለመውረስ ነው።
- አዳም በገነት እያለ ከመላእክት መዝሙርን ተምሯል።
- "ወጎብስተ መላእክቲሁ በልዑ እጓለ እመሕያው፡ የመላእክትንም እንጀራ ሰው በላ" ይላልና (መዝ. ፸፰፡ ፳፭)።
- በጌታ ልደት ሰውና መላእክት በጎብረት "ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብ" በማለትዘምረዋል። ሉቃ ፪፡ ፲ ፬

፩. ፬ መዝሙር በመጽሐፍ ቅዱስ

- እስራኤላውያን ከግብጽ ባርነት ነፃ ሲወጡ ዘምረዋል ።።ዘፀ. ፲ ፭፡ ፩- ፳ ፩
- እስራኤላውያን ጠላቶቻቸውን ባሸነፉ ጊዜ ዘምረዋል።። መሳ. ፭፡ ፩
- ክፉን መንፈስ ለማራቅ ዳዊት ዘምሯል።። ፩ኛ ሳሙ. ፲ ፮፡ ፲ ፬- ፳ ፪
- ኤልሳዕ ዘምሯል።። ፪ ኛ ነገ. ፫ ፡ ፲ ፫ ፡- ፲ ፮
- በጌታችን ልደት ሰውና መላእክት በጎብረት ዘምረዋል።። ሉቃ. ፪፡ ፲ ፬
- በፀሎተ ሐሙስ ከሥርዓተ ቁርባን በኋላ ሐዋርያት ዘምረዋል።። ማር . ፲ ፬፡ ፳ ፮
- ሐዋርያት በመከራ ውስጥ ሆነው ዘምረዋል።።ሐዋ ፲ ፮፡ ፳ ፭

ምዕራፍ ሁለት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና ፀዋትዋ ዜማ

፪. ፭ ቅድመ ክርስትና የነበረ ዜማ

- ኢትዮጵያ ከአምልኮተ እግዚአብሔር የተለየችበት ጊዜ የለም።
- በወቅቱ የነበረው ዝማሬ *ቃለ ማዕዘኒ* (ውርድ ንባብ) ይባላል።
- ታቦተ ጽዮን ወደ ኢትዮጵያ ስትመጣ ሌዋውያን ካህናትም አብረው ስለመጡ ዜማቸው፣ ማኅሌታቸውና የማኅሌት መሣሪያቸው ሁሉ አብሮ ወደ ኢትዮጵያ ገብቷል።፪ኛ ነገ. ፲
- ሌዋውያን ደግሞ ዋነኞቹ የመዝሙር ተጠቃሚዎች ነበሩ ዕዝ.፫፡፲።

፪.፪. ዜማ በክርስትና ምሥረታ ጊዜ

- ለምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ማስፈጸሚያ የሚሆን ክርስቲያናዊ ዜማ ነበራት።

- ነገር ግን እንደአሁኑ ጥልቀት፣ ምጥቀትና ርቀት ያለው፣ የተደራጀና የተቀነባበረ ዜማ አልነበረም።

- ከ ፭ ኛው መ/ክ/ዘ በኋላ ግን እግዚአብሔር ለታላቅ ሰማያዊ ጣዕመ ዜማ መገለጥ ቅዱስ ያሬድን መረጠ።

፪÷ ፫ የቅዱስ ያሬድ ታሪክና አነሣሥ

- ኢትዮጵያ፡- ብሉይ ከዳን
  - ሐዲስ ኪዳን
- “ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች” መዝ. ፷፰ ፴ ፡ ፴፩ ፡፡
- ቅዱስ ያሬድ ከአባቱ ከአብዩድ /ይስሐቅ/ ፣ ከእናቱ ከክርስቲና /ታውካልያ/ በ ፭፻ ፻ ፭ ዓ.ም. አክሱም ተወለደ፡፡
- ያሬድ ማለት ፡-
  - ርደት፣ ወሪድ ፣ መውረድ
  - ራዕየ ምሥጢር፣ ነፃሬ ጎቡአት
  - ጉብ ማለት ነው፡፡

የቀጠለ...

- ቅዱስ ያሬድ የብሉይና የሐዲስ መምህር ነበር፡፡
- ወደ ሰማይ ተነጥቆ ፷ ፬ ቱ ካህናተ ሰማይ ሲያመሰግኑ ሰምቶ ተመለሰ፡፡
- በታቦተ ጽዮን ፊት ቆሞ "ሃሌ ሉያ ለአብ፣ ሃሌ ሉያ ለወልድ፣ ሃሌ ሉያ ለመንፈስ ቅዱስ ቀዳሚሃ ለጽዮን ሰማየ ሣረረ ወበዳግም አርአዮ ለሙሴ ዘከመ ይገብር ግብራ ለደብተራ" ብሎ በልሳነ ግእዝ ዘመረ፡፡
- ይህችን ዜማ ቅዱስ ያሬድ "***አርያም***" አላት፤ ከመላእክት ወይም ከሰማይ የተገኘች ማለት ነው፡፡

፪. ፫. ፭ የቅዱስ ያሬድ የዜማ ድርሰቶች

ሀ. ድጓ፡- ረቂቅ፣ ስብስብ፣ ቁዘማ፣ ድግ(ትጥቅ)፣ መዝሙር ሐዲስ፣ ፍፁም ማለት ነው፡፡ (አብሠራ ገብርኤል ለማርያም ወይቤላ ተወልዲ ወልደ ሚካኤል መልአክ በክነፍ ፀራ መንጦላዕተ ደመና ሠወራ ንጽሕት በድንግልና አልባቲ ሙሰና ወልድ ተወልደ እምኔሃ)

ለ. ጸመ ድጓ፡- ጾም፣ ጸሎት፣ ምጽዋት (እምርት ዕለት በዓልነ ነያ አብርሃም አብ ዘተመነያ…)

ሐ. ዝማሬ፡- ማህበራዊ ምስጋና ማለት ነው፡፡

- ከድርገት በኋላ ይዘመራል፡፡
- ሐዋርያት ከቆረቡ በኋላ በጎብረት ዘምረዋል ማቴ. ፳፮ ፡ ፳ ፮ ፦ ፴ ፩ ፡፡ (ሑሩ በልዎ ለእገሌ ይቤለከ ሊቅ ……)

የቀጠለ...

መ. መዋሥዕት፡- አውሥአ(መለሰ) ፣ ምልልስ

- የጌታን ጥምቀት፣ ትንሣኤና ዕርገት
- የእመቤታችንን አማላጅነትና ክብር
- የጻድቃንንና የሰማዕታትን፣ የደናግልንና የመነኮሳትን ጥብዓትና ተጋድሎ የመላእክትን ተራዳኢነት
- የሙታንን ፀዓተ ነፍስና ዕረፍተ ነፍስ
- ምሳሌ፡ ደቂቅኒ እንዘ ይጸርሁ ወሕዝብኒ ኪያሁ ይሴብሑ ይኬልሁ ይጸርሁ ወይብሉ ሆሣዕና በአርያም።

ሠ. ምዕራፍ፡- ማረፊያ፣ መኖሪያ ማለት ሲሆን ውዳሴ ማርያም ዜማ፣ መስተጋብእ፣ አርባዕት፣ አርያም፣ ሠለስት፣ ክስተት፣ መወድስ የመሳሰሉትን ያጠቃልላል። (መንግሥቱ ዘለዓለም.....)

የቀጠለ...

በተጨማሪም፡-

- አንቀጸ ብርሃንን ከነዜማው
- ድርሰቱ የሌሎች ሊቃውንት ሆኖ ዜማው የሱ የሆኑ
  - አሥራ አራቱ ቅዳሴያት
  - ውዳሴ ማርያም

❖ **የቅዱስ ያሬድ የድርሰቱ ምንጮች፡-**

- መጽሐፍ ቅዱስ /ብሉይና ሐዲስ/
- መጻሕፍተ ሊቃውንት
- መጻሕፍተ መነኮሳት
- አዋልድ መጻሕፍት
- ገድላት
- ድርሳናትና ሌሎችም ናቸው::

፪. ፫. ፫ የቅዱስ ያሬድ የዜማ ምድቦች

፩.ግእዝ፡- ግእዘ ተጻዘ፣ነፃ ወጣ ፤ ነፃ መውጣት ማለት ነው፡፡

- በዜማነቱ ሲተረጎም ደግሞ ርቱዕ፣ የቀና፣ ፩ኛ ስልት፣ የመጀመሪያ
- ዜማ በእግዚአብሔር አብ ይመሰላል፡፡ (መዝሙር ሐዋዝ….)

፪. ዕዝል፡- የግእዝ ድርብና ታዛይ፣ ሁለተኛ ፣ ጽኑዕ፣ ጠንካራ

- ዕዝል አዘለ፣ አሰተአዘለ፣ አስተዛዘለ
- ከግእዝ ጋር ታዝሎ የመጣ ወይም የተገኘ ማለት ነው፡፡
- በእግዚአብሔር ወልድ ይመሰላል፡፡ (ነሥአ አብርሃም አዕጹቀ በቀልት..)

፫.ዓራራይ፡- ዓራኅራኂ፣ የሚያራራ ጥዑም፣ አሳዛኝ፣ ልብን የሚመስጥ ማለት ነው፡፡ (በጽዮን ንፍሑ ቀርነ..)

- በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ይመሰላል፡፡

የቀጠለ...

- የፊደል ቅርጽ የሌላቸው ስምንት የዜማ ምልክቶች አሉት።
- ምሳሌነታቸው ጌታችን ከልደት እስከ ዕርገት ላደረገው የመስቀል ጉዞ ነው።

፪. ፫. ፬ የቅዱስ ያሬድ የዜማው ምልክቶች

፩. ድፋት(∩)፡- ድምጽህንና አንገትህን ወደታች ርግጥ አድርገህ ደፍተህ፣ ትንፋሽህን ወደ ሆድህ ውስጥ መልሰህ አዚም ማለት ነው።ምሥጢሩ የክርስቶስን ከሰማየ ሰማያት መውረድ ያስረዳል። (ሠለስተ አስማተ.)

፪. ሂደት(~)፡- ስታዜም አታቁም፣ አታቋርጥ ምንም ነገር ሳይዝህ ሰተት ብለህ ሂድ ማለት ነው። ምሥጢሩ ጌታ በዚህ ዓለም እየተመላለሰ /እየተዘዋወረ/ ማስተማሩንና በተከሰሰም ጊዜ ከሐና ወደ ቀያፋ ወደ ሄሮድስና ጲላጦስ ምንም ሳይናገር መመላለሱን ያስረዳል። (እንዘ ዘል

የቀጠለ...

፫. ቅናት(√)፡- በዜማው መጨረሻ ያለውን አንዱን ፊደል ወይም ቃል ይዘህ አንገትህን ወደ ላይ አቅንተህ በማጋነን ድምፅ አዚመህ አቁም ማለት ነው፡፡ ምሥጢሩ አይሁድ በጌታ ላይ መቅናታቸውንና ጮኸው አሳልፈው መስጠታቸውን ያስረዳል፡፡

፬. ይዘት(●)፡- ዜማው እንደ ንባብ በፍጥነት ሲነገር ከመካከሉ አንዱን ፊደል ወይም ቃል ድንገት ያዝ አድርገህ አዚም ማለት ነው፡፡ ምሥጢሩ አይሁድ ጌታን መያዛቸውን በሌላም በኩል እግዚአብሔር ዓለምን በመታል እጁ የያዘ /አታዜ ዓለም/ መሆኑን ያስረዳል፡፡

የቀጠለ...

፫. ቁርጥ(r)፡- ድምጽህን በኃይል ቁርጥ አድርገህ ወደታች ትንፋሽህን አምቀህ ማዘምህን አቁም ማለት ነው፡፡ ምሥጢሩ አይሁድ ጌታን ቢያሰቃዩትም አዳምን ለማዳን መቁረጡን ያስረዳል፡፡ (ኢይፈርሆ ለእኩይ....)

፬.ጭረት(ሰ)፡- በዘማው መካከል ያለውን ንባብ አንዱን የፊደል ዘር ወይም ቃል ጎተት ወይም ሳብ አድርገህ አዚም ማለት ነው፡፡ ምሥጢሩ የጌታን ግርፋት /ሰንበር/ ያስረዳል፡፡ (ተሐነጺ በክብር...)

የቀጠለ...

፯. ርክርክ (:)፡- ዜማው እንዲረዝም በላይ በላዩ መጨመርና ማስረዘም ማለት ነው፡፡ ምሥጢሩ ጌታ ሲገረፍ የተንጠባጠበውን ደም ያስረዳል፡፡ (አ ገብርኤል ናዝዘኒ...)

፰. ደረት(◡)፡- ፊት ለፊት፣ ደረት ለደረት ቀጥ ብሎ በጉልህ ድምጽ በጉሮሮ የሚነገር የሚዜም ማለት ነው፡፡ ምሥጢሩ የጌታን ዕርገት ያስረዳል፡፡ (አሐዱ አብ ቅዱስ...)

- የኋላ ሊቃውንት የፊደል ቅርጽ ያላቸው ምልክቶች ጨምረዋል

፱. ድርሰ (ሰ)፡- ትንቢት ሁሉ መድረሱን፣ መፈፀሙን ያስረዳል፡፡

(ቀርቡ አርዳኢሁ ለአምላከ ጽድቅ)

፲. አንብር(ር)፡- ሁሉን ከፈፀመ በኋላ በአባቱ ቀኝ መቀመጡን ያስረዳል፡፡

(ሀገረ እግዚአብሔር)

የቀጠለ…

- እነዚህ ምልክቶች ***ሥርዓት ባለው መልኩ*** ተራ በተራ ሲጮሁ ያሬዳዊ ዜማን ይፈጥራሉ፡፡
- ባላቸው ምሥጢራዊ ትርጓሜ ነገረ መስቀሉን ከማሳሰብ በተጨማሪ የቅዱስ ያሬድ ዜማ እስከ አሁን ድረስ ለ፩፬፻፲፮ ዓመታት ተጠብቆ እንዲቆይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡

የቀጠለ...

ቤተክርስቲያን የያሬድን ዜማ የተቀበለችበት ምክንያት፡-

- ልቡናን በተመስጦ ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብ በመሆኑ
- የዜማው ይዘት የእግዚአብሔርን ቸርነትና መግቦት የሚያሳይና ከቅዱሳት መጻሕፍት የተውጣጣ በመሆኑ
- ቅዱስ ያሬድ በሥጋዊ ጥበብና ፍልስፍና ተራቅቆ የፈጠረው አለመሆኑ
- የዜማውና የመሣሪያዎቹ ሥርዓትና ምሥጢር ፍፁም መንፈሳዊ በመሆናቸው

የቀጠለ...

- ስለዚህ "እኔ ከአባቶቼ አልበልጥም" ፤ ኛ ነገ ፤ ፱፡ ፬ እንደተባለ እኛ ከአባቶቻችን አንበልጥምና ያቆዩልንን ዜማ ጠብቀን ልንጠቀምበት ይገባል።
- የእግኢአብሔርን ቃል የተናገሯችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ ፤ ፫፡ ፯
- አባቶችህ ያስቀመጡትን ድንበር አታፍርስ ምሳ. ፳፪ ፳፪፡ ፳፪ ፳፰

፪. ፩ ማኅሌትና ምሥጢሩ

- ማኅሌት - ኅለየ፣ ዘመረ፣ አመሰገነ
- ይዘቱና አፈፃፀሙ "አቋቋም" ይባላል።
- ሰማያዊና የጌታችንን መከራ በዐይነ ኅሊናችን እያየን ወደ ንስሐና እግዚአብሔርን ወደ ማወቅ የሚያደርሰን ነው።
- በማኅሌት ፲ ደረጃዎች ይከናወናል።
- "ወበመዝሙር ዘአሠርቱ አውታሪሁ እዜምር ለከ፤ አሥር አውታር ባለው መዝሙር እዘምርልሃለው።" መዝ. ፺፪ ፡ ፫ ያለውን መሠረት በማድረግ ነው። እነርሱም፡-

የቀጠለ...

፩. መቃኘት፡- አይሁድ ጌታን ለመያዝ ይሁዳን አመልካች አድርገው ለመፈለጋቸው ምሳሌ

፪. መቀበል፡- የአይሁድ ጭፍሮች ጌታን ከይሁዳ ተረክበው ውሳኔያቸውን የመፈፀማቸው ምሳሌ

፫. መምራት፡- ሊቀ ካህናት ሐና ጌታን እንዲይዙ ጭፍሮቹን የመላኩ ምሳሌ

፬. መመራት፡- የአይሁድ ጭፍሮች በተሰጣቸው ትዕዛዝ መሠረት ጌታን ይዘው መጀመሪያ ከሊቀካህናቱ ሐና ፊት ለማቅረባቸው ምሳሌ

የቀጠለ...

፫. **ዝማሜ**:- መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሐና ወደ ቀያፋ፣ ከጲላጦስ ወደ ወደ ሄሮድስ መመላለሱንና መውደቁን ያመለክታል። በመቋሚያው መሬቱን መምታታቸው አይሁድ የጌታን ራስ በዘንግ መምታታቸውን ያመለክታል።

፮. **ቁም /ንዑስ መርግድ/** :- አይሁድ በሕጋቸው ፵ ሲገርፉት ረጋ ብለው መጀመራቸውን ያመለክታል

፯. **ዐቢይ መርግድ**:- አይሁድ በሕጋቸው ፵ ሲገርፉት ረጋ ብለው ከጀመሩ በኋላ ግርፋቱን ለማክበድ ተሳሳትህ መልስ እያሉ ፵ ፮ ፻ ፵ ፮ ጊዜ እንደገረፉት ለማዘከር ነው።

የቀጠለ...

፰. **ጽፋት፡-** ከበሮውንና ጸናጽሉን በማሳጠር የሚዘመር ነው፡፡ ጌታ በጥፊ መመታቱን ለማሰብ ነው፡፡

፱. **ድርብ ጽፋት፡-** በጸናጽልና በዜማ ቃና /ጉሮሮ/ ከተራው ጽፋት በከበሮ አመታት ለየት አድርጎ መዘመር ነው፡፡ አይሁድ ጌታን ደጋግመው በጥፊ እንደመቱት ለማሰብ ነው፡፡

፲. **የጭብጨባ ጽፋት፡-** ከተራው ጽፋት ጋር በጉሮሮው / በአጣጣሉ/ በመጠኑ ፈጠን ፈጠን አድርጎ በጸናጽል ፈንታ እያጨበጨቡ በከበሮ መዘመር ነው፡፡ ምሳሌውም ከላይ በ "፰ " ና በ "፱ " እንደተገለጸው ነው፡፡

እንግዲህ የመዝሙሩ እንቅስቃሴ ሁሉ ስለ ክርስቶስ መከራ መስቀል ሰፊ ትምህርት የሚሰጥ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

፪.፭ የዜማ መሣሪያዎች


- የቤተክርስቲያን የዜማ መሣሪያዎች፡-
  - ነፍስና ሥጋን በመንፈሳዊ ሐሴት የሚመሉ
  - በመላእክት ዘንድ ያሉ
    - በተመስጦ ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሱ ናቸው፡፡
- ቤተክርስቲያን የመጣውን ሁሉ አትቀበልም

ከነዚህም መካከል ጥቂቶቹ፡-

፩. ከበሮ፡- ምሳሌነቱ፡

- ማንገቻው የተገረፈበት የጅራፉ
- የጠፍሩ ጥልፍልፍ ሲገረፍ የወጣበት ሰንበር /ምልክት/
- ቀይ ግምጃው ቀይ ከለሜዳ የመልበሱ
- ውስጡ ባዶ መሆኑ የመቃብሩ ምሳሌ
- አንድም የከበሮው ሰፊው ክፍል የመለኮትን ሰፋሕነት ጠባቡ የትስብእትን ውሱንነት ያመለክታል፡፡

ከበሮ



ምሉዕ በኩለሄ የዋሃን ኣግዚኣብሔርን
በአንገቱ ገመድ አስገብተው ያንገላቱትን ያጠየቃል::
ጌታችንን በገረፉት ወቅት ከሰውነተ የወጣውን ሰንበር ሲያስታውሰን
ከበሮ የጌታችን ምሳሌ ነው
ወልድ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት መወሰኑን ይገልጣል

የቀጠለ...

፮. **ጸናጽል፡-**

- ፪ ቱ ዘንጎች የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ምሳሌዎች ሲሆኑ፣ ቅጠሎቹ ደግሞ የፍጥረተ ዓለም ምሳሌ ነው፡፡
- ኪደነ ኖኅን አስብና በኃጢአታችን አታጥፋን ማለት ነው፡፡
- አንድም ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ ያየው መሰላል አምሳል፡፡

ጸናጽል



በያዕቆብ መሰላል ☐ፋን ላይ ያለ☐ እ☐☐አብሔር፡ መስቀል፡በቀራንዮ የተሰቀለ☐ ☐ቻችን ኢየሱስ ክርስቶስ

በያዕቆብ መሰላል እ☐☐አብሔር ያ☐ጠት ☐ፋን፡ የኖህ ቀስተ ደመና፡ የቀራንዮ ተራራ

በያዕቆብ መሰላል ☐ሚላእክት ፡ ፫ ቢሆኑ የ፫ቱ አእማድ ም☐ር፡ ፯ ቢሆሉ ☐፮ቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን

☐ያዕቆብ መሰላል መዉጫና መዉረጃ ፡ ☐☐ቅረ እ☐☐አብሔርና የፍቅረ ቢጽ

☐ያዕቆብ መሰላል ምሰሶ ፡ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን

የህገ አማ☐አብሔር ፡ የፍቅር ምሳሌ

የቀጠለ...

፫. መቋሚያ፡-


ምሳሌነቱ፡

- የበትረ ሙሴ
- ጌታችን የኃጢአትን ባሕር ከፍሎ ያሻገረበት

የመስቀል ምሳሌ ነው፡፡

- ቅዱስ ያሬድ በማኅሌት ፤ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ደግሞ በሰዓታት ጊዜ መቋሚያ እንዲያዝ ሥርዓት ሠርተዋል፡፡

መቋሚያ



ነገረ መስቀሉን
እንድናዘክር ያደርጋል

ጌታችን መስቀል ተሸክሞ

መንገላታቱን


የቀጠለ...

፬. በገና፡- አሥር አውታሮችና ሁለት ምሰሶዎች አሉት፡፡

- ሁለቱ ምሰሶዎች የፍቅረ እግዚአብሔርና የፍቅረ ቢጽ አንድም የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ምሳሌ
- አሥሩ አውታሮች ደግሞ የአሠርቱ ቃላተ አሪት አንድም የአሥሩ የቅድስና ማዕረጋት ምሳሌ ፡፡

፩ኛ ዜና ፲ ፳፫፡ ፳፭ ፩ ፣ ፩ ኛ ሳሙ ፲ ፮ ፡፲ ፮ ፡- ፳፭ ፪ ፣ ፪ ኛ ነገ. ፫፡ ፲ ፬ ፣ መዝ. ፺ ፩፡ ፫

በገና





በብሉይና በሐዲስ ይመሰላሉ

አሥሩ አውታሮች በአሥርቱ ትዕዛዛት ይመሰላሉ

♦ፍቅረ ቢፅና ፍቅር **እግዚአብሔር** አሥርቱ ትዕዛዛት አንደሚፈፀም ጌታ ያሰተማረውን ያጠይቃል።

የቀጠለ...


፫. መሰንቆ፡- ሰንቀወ (አስጨኸ)፣ ከረከረ

- መሰንቆ የሃይማኖት ምሳሌ፡- አንድ አውታር አለው - አንዲት ሃይማኖት
- ቅዱስ አትናቴዎስ "መሰንቆ ይእቲ ሃይማኖት እንተ ለብስዋ ሰማዕታት፤ መሰንቆ ሰማዕታት ገንዘብ ያደረጓት ሃይማኖት ናት::" ብሏል::
- በ ፫ ጣቶች ይነካካል - ሃይማኖትም በ ፫ ቱ አዕማደ ምሥጢራት ትተነተናለች::
- አንድም መሰንቆ የእመቤታችን ምሳሌ
- ድምፁ የምስጋናዋ፣ ዕጣኑ የጌታ

ኢዮ ፳፩ ፭ ፤ ፲ ፪ ፣ መዝ. ፺ ፭ ፡ ፫ ፣ መዝ÷ ፭ ፻ ፵ ፡ ፫ ፣፭ ኛ ዜና ፲ ፫፡ ፲ ፮

መሰንቆ

❑የኖንቃል ኪዳንን ያጠይቃል



ነገር መሰቀሉን እንድናስታወሰው

የአንዲት ሃይማኖት ምሳሌ ነው

መሰንቆ **የእመቤታችን** ምሳሌ ነው
ዕጣኑ **የክርስቶስ** ድምፁ ደግሞ
የምስጋናዋ

ቅዳሴ ኣትናቴዎስ መሰንቆ ይዕቲ ርትዕት ሃይማኖት እንተ ሰበክዎ ሐዋርያት
መስንቆ ያልኪት ***ሐዋርያት*** የሰበኪተ ቀጥተኛ ሃይማኖት ናት

የቀጠለ...

፮. **መለከት**:- እንደ ጥሩንባ ያለ ነው

- ዕለተ ምጽአትን እናስብበታለን

- በሐዲስም በብሉይም ተጠቅሷል። መዝ. ፷ ፯ ፶ ፡ ፫ ፣ ፩ኛ ተሰ. ፬፡፲፮


፯. **እንዚራ**:- ከዋሽንት ሰፋ ያለ ሲሆን የሚነፋውም ትንፋሽን በአንድ እጅ ብቻ በመያዝ ነው።

-የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት ሲከብር ለክብሩ ይነፋ ነበር

መዝ. ፷ ፯ ፶ ፡ ፬ ፣ ኢዮ. ፩፡፲፪

፰. **ዋሽንት**:- አራት ቀዳዳዎች አሉት - የ፬ቱ ወንጌላውያን ምሳሌ

ዋሽንት



አራቱ ቀዳዳዎች የአራቱ ወንጌላውያን ምሳሌዎች

የወንጌል ምሳሌ ነው

ወንጌልም ወልደ እግዚአብሔር ተወለደ ዲያብሎስ ተሻረ የሚልን የምሰራች ትናገራለችና

፪. ፯ መዝሙር ለቅዱሳን

- **ምስጋና ለቅዱሳን፡-** ቅዱሳን መላእክት፣ ቅዱሳን ሰዎች ምስጋና ይገባቸዋል።
- **ምስጋና ለዕለታት፡-** እግዚአብሔር ድንቅ ታምራቱን የሠራባቸው ዕለታት
- **ምስጋናና ክብር ለቦታዎች፡-** ቅዱሳት መካናት

❖ነቢዩ ዳዊት ስለኤፍራታ ቤተልሔም፣ ስለዮርዳኖስ፣ ስለጽዮን ዘምሯል።

መዝ. ፸፻፴፩፡፮፣ ፸፻፲፫፡፫፣ ፸፻፴፮፡፮

ምዕራፍ ሦስት

የዘመናችን የአማርኛ
መዝሙራትና ችግሮቻቸው

፫. ፭ አጀማመር

- ሁለት መነሻዎች አሉ፡-የእናቶች የአማርኛ መዝሙራት
  - የካህናት ማኅሌተ ገንቦ
- በካሴት የተጀመረው ፲፱፻፹ዎቹ ገደማ ነው፡፡
- በወቅቱ ወጣቱ ፡- በዘመናዊ ፍልስፍናና
  - በመናፍቃን ትምህርት ተታሎ
  የካደበት ነበር
- መንፈሳዊ ማኅበራት ተቋቁመው ነበር - ወጣቱን ለመመለስ
- ለአማርኛ መዝመራት መጀመርና እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡

፫. ፪ እድገት

❖በወቅቱ የነበሩ ችግሮች በመዝሙራችን እድገት ላይ ከፍተኛ ችግር አድርሰዋል፡፡ ለምሳሌ፡-

- ፖለቲካዊ ችግሮች - ፋሽስት ኢጣሊያ
  - የሥርዓት ለውጦች
- የመናፍቃን የረቀቀ ስልት - ሰርገው በየሰ/ት/ቤቶች መግባት
- የልምድ ማነስና ስለመዝሙር አገልግሎት የግንዛቤ አነስተኛነት
- የመዝሙር ደራሲያን ቁጥር ውስንነት (የሰንበት ት/ቤት ወጣቶችና ካህናት በተለያዩ ክበቦች መግባት)
- የተሐድሶዎች ጠንካራ እንቅስቃሴ

፫. ፫ ችግሮች

- መዝሙር ፡- ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋት

  - ምዕመናንን ወደ እግዚአብሔር ለማቅረብ ታላቅ እገዛ አድጓርል፤ በተለይ ቀደም ያሉት መዝሙራት ፡፡

- ነገር ግን በዚያው አልቀጠለም
- እያደር እየላላ፣ ጣዕሙ እየቀነሰ፣ ለዛው እየጠፋ፣ ላጎዩም እየደፈረሰ መጥቷል፡፡
- ችግሩን እንደሚከተለው እንመለከታለን……

- ለመሆኑ አርቶዶክሳዊ መዝሙር ማለት ምን ማለት ነው???

፩. የቤተክርስቲያንን እምነት /ዶግማ፣ ቀኖናና ትውፊት/ የጠበቀ

፪. የመዝሙር መሣሪያዎቹ ቤተክርስቲያን የምትቀበላቸው ሲሆኑ

፫. ዜማው ያሬዳዊ ሲሆን

፫. ፫. ፩ የኦረቶዶክሳዊነት ችግር

በኦርቶዶክሳዊነት ዙሪያ ያሉትን ችግሮች እንመልከት!

ሀ. ከግጥም ይዘት እንፃር

- የግጥሙ ይዘት፡-
  - የቤተክርስቲያንን ዶግማ፣ ቀኖናና ሥርዓት የጠነቀቀ
  - በምስጢር የዳበረ (ምሳሌ፡ ማርያም ፊደል የኾሉ መማሪያ በንጽሕና ተጽፋለችና)
  - የሥነ ግጥም ባሕርያትን የያዘ (እምቅነት፣ ቁጥብነት፣ወ.ዘ.ተ.)
  - ጠንካራ መልእክት የሚያስተላልፍ
  - መልእክቱ ዘመኑን የዋጀ
  - ከቤተክርስቲያን አስተምህሮ ጋር የማይጋጭ

የቀጠለ...

- ዓለማዊነትንና ዘመናዊነትን (የሥጋን ሥራና ፋላጎት) የማያስፋፉ
- አስተማሪና በተመስጦ ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኝ
- ወደ ንስሐ፣ ወደ ቅዱስ ቁርባንና ወደ ጥልቁ መንፈሳዊ ባሕር የሚመራ መሆን አለበት።።

- ነገር ግን አሁን አሁን እየታዩ ያሉት መዝሙራት አብዛኛዎቹ ይዘታቸው፡-
  - ቁሳዊነትን /ዓለማዊነትን/ የሚስፋፉ
  - ወደ ግላዊነት የሚያደሉ

የዘመናችን የአማርኛ መዝሙራት ችግሮች

ሀ.ከግጥም ይዘት እንፃር

ለምሳሌ: ጻድቃን ሰማዕታት ቅዱሳን ሁላችሁ
እኔን ኃጥኡን ሰው አማልዱኝ ባካችሁ
<u>አይምረኝምና</u> እኔን አምላካችሁ

ይህ ከምልጃ ትምህርታችን የወጣ ነው። እግዚአብሔር አልምርም ስለሚል አይደለም ምልጃ ያስፈልገው። ይህን ኃጢአት ይገፍ በፊትህ ልቀርብ አይቻለኝም በማለት እንጂ።

ክብር ለሚገባው ክብር አለመስጠት /ማቆላመጥ/

ርዕስ፡- የኔ ናርዶስ

የሳሮኑ ጽጌሪዳ ያገኘሁህ ምድረበዳ
ስለፍቅርህ ታምሜአለሁ
በመስቀልህ ታክሜአለሁ

ግጥሙ ላይ የሚታየው ችግር አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከፍቅሩ ብዛት የታመመውትን አድኖአል። ከሞት ወደ ሕይወት አምጥቶአል። /ዮሐ፡- 3÷16/ የመዝሙሩ ግጥም ግን "ስለ ፍቅርህ ታምሜአለሁ" በማለት ስለተቃራኒ ጸታ ፍቅር አገላለጽ ተገልጸአል።

ዝናው በአለም

ዝናው በአለም ተሰማ

የዘካርያስና የኤልሳቤጥ ኮርማ

ርዕስ፡- አድጌአለሁ

ድክ ድክ እያልኩኝ ከቤትህ ስገባ
ታቅፈኛለህ በፍቅር ስመህኝ አባባ
ለካ አስበኸኛል ልሆን በመቅደስህ
ጌታህን እንዲከብር ቆሜ ከመድረክህ

ግጥሙ ስለ ጻድቁ አቡነ ተክለሃይማኖት የተገጠመ ነው። ቅዱሳንን አበው አባት የምንላቸው አባትነታቸው በስጋ ሳይሆን በመንፈስ ነው። የግጥሙ ቃል "ስመኸኝ አባባ" የሚለው በስጋ አባት የሚነገር ቃል ተጠቅሞአል።

. የተሳሳተ ትርጉም /ያገላለፅ ችግር/

ከቋንቋ እና ስነጽሑፍ አንጻር

ርዕስ፡- ያላንተ ለኔ

ቀሳፋያችን ቀስፈኸዋል
ያንን ጭንቁን ቀን አልፈነዋል
ነገም ያንተ ነው አዲሱ ቀን
እንዘምራን ስትናፍቀን

እርሱ ሱናፍቅ ብቻ ሳይሆን ሁልጊዜ ነው የምንዘምርለት

ርዕስ፡- አቤቱ ለአንተ

ለዝናም አይደለም ወይም ለሞቅታ
የምዘምርልህ ለአምልኮ ነው ጌታ

የቃላት አመራረጥ ችግር - ተራ አነጋገር

ርዕስ፡- በንፅህ ደምህ

ቀናብለናል በክብር
አንገቱን ደፍቶ በክብር
ስለኛ ብዙ ሆነልን
<u>የብርሃን አክሊል ደፋልን</u>

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የብርሃን አክሊል
ተጉናጽፏል እንጂ የብርሃን አክሊል አልደፋም።
የደፋው የብርሃን ሳይሆን የእሾህ አክሊል ነው"

. ተፋልሶ ያለባቸው ቃላት መጠቀም

ርዕስ፡- በአንባ ፈረስ ላይ ሆነህ

በአንባ ፈረስ ላይ ሆነህ በራዕይ የታኸኝ

ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ወዳጄ ድረስልኝ

ኢየሱሰ የማሪያም ልጅ አንድዬ ንገስልኝ

ይሄ የመዝሙር ግጥም ሁለት ነገሮች እንደ ችግር ይታዩበታል፡፡

1ኛ. ኢየሱስ ክርስቶስ በአንባ ፈረስ ላይ ተቀምጦ በራእይ አየሁት ይላል፡፡ ሁለተኛው "ንገስልኝ" የሚል ቃል ተካቶበታል፡፡

ለእርሱ ንገሥልኝ አይባልም ለፍጡር እንጂ ንግስናው የባህሪው ስለሆነ ነው፡፡ ንጉስ ዳዊት "እግዚአብሔር ግን ከዓለም አስቀድሞ ንጉሥ ነው" ብሏል /መዝ፡73(74)÷12

ምስጋና ጀመረ

በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ምስጢር እያስማማ
ምስጋና ጀመረ በጽዮን ከተማ
ለሶስቱ ሥላሴ በሶስት አይነት ዜማ

አ ክርስቶስ አ አምላክ ግሩም ነህ

ዮሐንስ እንዳለ ክርስቶስ

ጥምቀት ለንስሐ ክርስቶስ

እታጠበዋለሁ የጎንህን ውኃ

መጥምቁ ዮሐንስ

አንገት ተለይቶ ከሌላ ሰውነት

እንዴት ያስተምራል <u>አስራ ሁለት ዓመት</u>

ርዕስ፡- ዕንባን አልሠፍርም

የእነ አፍኒንን ድንኳን ተጸየፈች ነፍሴ
ውስጤ ባያርፍ ነው በፊትህ ማልቀሴ
ከስደት መልሰህ የሾምከኝ በፀጋ
አበርታው አምላኬ ልቤ እንዳይሰጋ

የመዝሙሩ ግጥም የእነ አፍኒንን ድንኳን ተጸየፈች ነፍሴ ይላል እግዚአብሔር የተጸየፈው ድንኳኑን ሳይሆን የአፍኒንና የፊንሃስን ስራ ነው

ርዕስ፡- ተሰቀለ

ተጠማሁ እያለ ሲናገር ሰምተው
ሐሞትና ከርቤ ሰጡት ቀላቅለው
ተቀብሎ ቢቀምሰው በጣም የቆመጠጠ
ነፍሱን ለሁላችን አሳልፎ ሰጠ

ጌታን አይሁድ በሰቀሉት ሰዓት ጌታ "ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ ብሎ በታላቅ ድምፅ ሲጨኽ"/ማቴ፡-27፡46/ ከቆሙት መካከል "አንዱ ሰፍነግ ይዞ ሆምጣጤ ሞላበት በመቃም አድርጎ አጠጣው" /ማቴ፡-28፡47/ በወንጌሉ አጠጡት እንጂ ተቀብሎ ጠጣው የሚል ቃል የለውም።

የኦርቶዶክስ

ካልባረከኝ አለቅህም

ካልባረከኝ አለቅህም አምላኬ ነህ ለዘላለም
ጌታዬ ነህ ለዘላለም
አዝ.....
ሊነጋ ሲጀምር ሰማዮ ሲቀላ
ወዴት እሔዳለው ነፍሴ እንዲህ ዝላ
እያለቀስሁ ሁሉ እከተልሀለሁ
እጅህን ዘርጋልኝ በረከት እሻለሁ
አዝ.....
ለብቻዬ ልቅር ፈቃድህ ከሆነ
ሌላውን አልሻም ሕይወቴ ከዳነ
ሲሆን እስከ ንጋት ልታገልህና
ስደደኝ ጌታዬ ሕይወቴን ባርክና
/አምላክ/ /2/
አዝ.....
ታምሜ ስላደርኩኝ ሞልቶኝ በረከትህ
አየሁ ጌታዬ ዛሬስ ፊትለፊትህ
ድምፄን አሰምቼ አልኩኝ ጽንኤል
ስሜም ተለወጠ ተባለ እስራኤል/2/
አዝ.....

የፕሮቴስታንት

ካልባረከኝ አለቅህም

ለብቻዬ ልኖር ፈቃድህ ከሆነ
ሌላው አይገደኝም ህይወቴ ከዳነ
ሲሆን እስከ ንጋት ልታገልህና
ስደደኝ ጌታዬ ሆይ ሕይወቴን ባርክና
አዝ.....
በመንበርከክ ብዛት በጸሎት ትግል
ፈቃድህ ከሆነ ጉልበቴ ይዛል
እያለቀስኩ ይሆን እከተልሀለሁ
እጅህን ዘርጋብኝ በርከት እሻለሁ
አዝ.....
ሊነጋ ሲጀምር ሰማዩም ሲቀላ
ወዴት እሔዳለሁ ነፍሴ እንዲህ ዝላ
ሕይወቴን ብቻ ባርክ ሌላ አልመኝም
ስም እንደው ቀሪ ነው ስም አያድነኝም
አዝ.....
እንደ ያዕቆብ ዛሬ ጨኽቴን ስማና
ስደደኝ ጌታሆይ ህይወቴን ባርካና
ፈቃድ ከሆነ ስሜንም ለውጠው
ሰው እንዳለው ሳይሆን አንተ እንደወደድከው

ለ. ከዜማ አንፃር

- ዜማው ያሬዳዊ ብቻ መሆን አለበት፡-
  - በያሬዳዊ ምልክቶች መሠረት የተጫኸ
  - ከቮቱ የቅዱስ ያሬድ የዜማ ምድቦች ውስጥ በአንዱ የሚካተት እና
  - የያሬድን የአቀራረብ ሥርዓት የተከተለ ማለት ነው፡፡

- የዘፈንን ዜማ፡-የተወሰደዉ ከቤተክርስቲያን ነው በሚል ሐብቷን የማስመለስ እንቅስቃሴ አድርጎ መቁጠር
- የተወሰዱትም፡- ከአለማዊ ዘፈን፡ከባህላዊ ዘፈን እና ከለቅሶ ሙሾ
- ምሳሌ፡- ሃና ዘመዴ ሃና ዘመዴ ሃና ዘመዴ
እርሷ ተስላ ወልዳ ለእኛ ሰጠችን መዳኛ
የሚለዉ &
እንዲያዉ የምሩ የምሩ እንዲያዉ የምሩ
ከሚለዉ የሰርግ ዘፈን &

2 .ይሰግዱ ለኪ ይሰግዱ ለኪ

ወይትመሐለሉ በቅድመ ገጽኪ ይሰግዱ ለኪ

የሚለዉ

አልማዝ ምን እዳ ነዉ/2/

የምንገናኘዉ በየትኛዉ ወር ነዉ

ከሚለዉ የሰርግ ዘፈን

3.እመኑ በርሱ ድንቅ ያደርጋል ጌታ

የሚለዉ

በላያ በላያ በላያ በላያ

ከሚለዉ የሰርግ ዘፈን

4 ኧረሰይ አማኑኤል
አማኑኤል አማኑኤልኧረሰይ አማኑኤ ል

የሚለዉ
ምነዉ በአፈሩላይ
ከሚለዉ የለቅሶ ሙሾ ዜማ

5 ሃመልማል ሃመልማል ሃመልማለወርቅ ልብሱ የእኛ ሙሽራ
የሚለዉ
ብርአምባር ሰበረልዎ ብርአምባር ሰበረልዎ
ከሚለዉ የሰርግ ዘፈን

6 መላዕክቱ በፊቱ ይቆማሉ የሚለዉ
ና ሙናዬ ሙናዬ ለኔ ናና ከሚለዉ ዘፈን

7 ቋንቋየነሽ ድንግል መግባቢያየ
የሐረሯ ቆንጆ ነይልኝ

የራስን ድርሰት እንዴት ያሬዳዊ ማድረግ ይቻላል???

- ሁለት መንገዶች አሉ ፡-

፩. *ከቅዱስ ያሬድ የዜማ ድርሰቶች ላይ በአንዱ የሰማነውን ዜማ በወጥነት በመውሰድ የራሳችንን ግጥማዊ ድርሰት በዚያ ዜማ በመዘመር/በመጮኽ/ ያሬዳዊ ማድረግ ይቻላል።።*

<u>ለምሳሌ</u>፡- ኢትግድፈነ አትግድፈነ ወኢትመንነነ አምላከ ሰላም ተራድአነ

የቀጠለ...

፪. ከተለያዩ የዜማ ድርሰቶቹ የዜማ ቅንጣቶችን በመገጣጠም

- የዜማ ቅንጣቶች ግን በቃላት ደረጃ እንጂ በሆሄያት ደረጃ አይደለም፡፡

  ለምሳሌ፡- ሰው ለሰው ቢፋቀር ምነው ሰው ለሰው ቢፋቀር ምነው

- አሁን አሁን ዜማ ሁሉ ከያሬድ አይወጣም በሚል ፈሊጥ በቤተክርስቲያን ያልነበረና ታይቶ የማይታወቅ ዜማና በሆታና ጭፈራ የታጀበ የዝማሬ ሥርዓት እየታየ ነው፡፡

ሐ. ከቅንብር አንፃር

❖በዚህ ረገድ ከሚታዩ ችግሮች መካከል፡-

- ከተፈጥሮ ድምፅ ውጭ የሆነ የጥቅስ ንባብ
- አለባበስ (የተለያዩ አልባሳትን መቀያየር፣...)
- በተለያዩ አልባሌ ቦታዎች፣ መናፈሻዎች፣ ወንዝ ዳርና የግለሰብ ቤቶች ውስጥ መቀረጽ

የቀጠለ...

- የመናፍቃንን ፊልም ለቅንብር መጠቀም
- ከመንፈሳዊ ሕይወት (ነገረ ድኅነት) ይልቅ የሥጋዊ (ምድራዊ) ሕይወትን የተመለከተ መሆን
- የክሊፖች መብዛት
- ሥርዓት የሌለው አሸባሸብ፤ ዝላይና ጭፈራ ያለበት መሆን
- የቤተክርስቲያንን ለዛና የተረጋጋ ቋንቋ ያላገናዘበ የዓለም ሁከትና ጩኸት መምሰል
- ወ.ዘ.ተ.

የቀጠለ....

- ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን ሳይጠብቁ በስምዋ መነገድ
- በየሀገሩና በየከተማው እየዞሩ በሞንታርሽ ጀሮ የሚበጥስ የመዝሙር ትውውቅታና ሽያጭ ማድረግ
- በታላላቅ ጉባኤያት እየተገኙ የቤተክርስቲያንን መድረክ ማስተዋወቂያ ማድረግ
- በየንግሥ በዓሉ እየዞሩ ሥርዓተ ቅዳሴንና ስብከተ ወንጌልን ማወክ የተለመዱ ተግባራት ሆነዋል፡፡

መ. ከመዝሙር መሣሪያዎች አንፃር

- ቤተክርስቲያን እንድንጠቀምባቸው ከፈቀደችልን ውጭ ሌሎች መሣሪያዎችን መጠቀም ከቤተክርቲያኗ ጎብረት ይለየናልና ልንጠነቀቅ ይገባል።

፫. ፫. ፪ ዘመናችንን ያለመወጀት ችግር

- ዘመናችን "ክፍት" ወይም "የተጋለጡ" ሁነው የሚገኙትን ሀብቶችን ሁሉ የሚለውጡ ፍልስፍናዎች የነገሰበት ዘመን ነው፡፡

- ዓለማዊነት /Secularism/ - የአብያተ ክርስቲያናት ችግር
- ሉላዊነት - ሃይማኖቶችን ሁሉ ወደ አንድ ለማምጣት ካልተቻለ
  - "ሁሉንም በማጥፋት አንድ ማድረግ "
  - ሃይማኖተኞችን ቀስ በቀስ በቅየጣ /Syncretization/ ወደ ዓለማዊነት መቀየር

የቀጠለ…

- "በአሁኑ ሰዓት መናፍቃንም ሆኑ ዓለማውያን የእኛን መዝሙር እያዳመጡት ነው!" ለምን?

→ ወደ እውነተኛው ዝማሬ /ተመስጦ/ አሸጋግረናቸው ነው? ወይስ መዝሙሩን ከዘፈኑ አቀራርበንላቸው?

→ ስለዚህ ከራሳችን ሀገር ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እያዩ መፍትሔ መስጠት ያስፈልጋል።

፫. ፬. የችግሮች መንስኤዎች

፭. የፖሊሲ አለመኖር

ዘመኑን የዋጀ ፖሊሲና ኤዲቶሪያል ቦርድ አለመኖር

፮. የባህል ተጽእኖ

- ከእኛ ውጭ በሆነ ባህል መማረክ
- የፕሮቴስታንት የመዝሙር ባህል
- ዘፈን

የቀጠለ...

፫. ለዘመናዊነት ያለው የተዛባ አመለካከት

- አንድን ነገር ዘመናዊ ማድረግ ማለት ያለን ነገር ሌላው ሙለ በሙሉ እንዲቀበለው ማድረግ ፤ ካልተቻለ ደግሞ ቢያንስ ለሐሳቡ ተገዢ እንዲሆን ማድረግ ነው::
- ታዲያ መዝሙራችን እንደዚህ ያለ ተጽዕኖ እየፈጠረ ነው ወይስ እየተፈጠረበት?

፬. የትምህርት ማነስ

- ለዘማሪነት የሚያበቃ ትምህርት አለመኖር፡፡
- በመንፈሳዊ ኮሌጆች በትምህርት መስክ/Faculty or Department/ ዜማ፣ ንባብ፣ ፖሊሲ፣ ትውፊት፣ ባህልና ነገረ ሃይማኖት፣ የሥነ ጥበብ/ግጥም፣ ሥነ ጽሑፍ፣... ወ.ዘ.ተ. / የሚሉትን የትምህርት ዓይነቶች ያካተተና ምስክርነት /ሰርተፍኬት፣ ዲፕሎማ፣ ዲግሪ፣ ፪ኛ ና ፫ኛ ዲግሪ/ የሚሰጥበት ሆኖ መኖር ነበረበት፡፡
- ያሬዳዊ ዜማ ለመዘመር - ያሬዳዊ ዜማን መማር

- ቢያንስ ትንሽ ንባብ፣

የዜማ ስልትና ቃና

፮. ግዴለሽነት

- በ ፮ቱ አካላት ጎልቶ ይታያል፡-
  - በዘማርያኑ
  - በደራሲያኑ
  - በአሳታሚው
  - በቤተክርስቲያን አባቶች
  - በምዕመናን

፮. ዘፈን

- መወዛወዝ፣ መዝለል፣ መፈንጨት፣ እስክክስ ማለት
- ስለ ሥጋ ስሜትና ስለ ሥጋ እርካታ ያቀነቅናል
- ማቴ. ፲፬

፮. ፩. በተክርስቲያን ዘፈንን ለምን ትከለክላለች?

- ፍጡር ለፍጡር የሚያቀርበው በመሆኑ - አምልኮ ጣዖት
- ሥጋዊ ደስታን በመፍጠርና ወደ ዝሙት ይገፋፋል።
- የአጋንንት ሥራ ነው፤ "... በዚያ አጋንንት ይዘፍናሉ።" ኢሳ. ፲፫ ፡፳፩

"... እየዘፈኑም ከአጋንንት ጋር ይጫወታሉ። አጋንንተም ጨዋታቸውንና ዘፈናቸውን ያደንቁላቸው ነበር።" ፩ኛ መቃ. ፴፩፡፳፪ -፳፰

- ዘፈን የሥጋ ሥራ በመሆኑ ኃጢአት ነው። ገላ. ፭ ፡፳፩፣ ሮሜ. ፲፫ ፡ ፲፫& ፩ኛ ጴጥ. ፬፡፫

የቀጠለ...

- መንፈሳዊነትን ይጋፋል፡፡ ለጸሎት፣ ለመዝሙር፣ ለምስጋናና ለመንፈሳዊ ነገር ሁሉ ያለንን ጊዜ፣ ፍቅርና ትጋት ይሻማል፡፡
- ርኩስ መንፈስን ያቀርባል፡፡

፯ ፪ የመናፍቃን "መዝሙር"

- አንድ መዝሙር መዝሙር ለመባል፡-

፩. በሚያምን ሰው ሊዘመር ይገባል፤

"ሃይማኖትን ምግባርና ሃይማኖት ከተሰማሙለት ሰው ይማሩ ዘንድ ይገባል" እንዲሉ አበው፡፡

፪. በሥርዓት ሊዘመር ይገባል፡፡

- መናፍቃን ሃይማኖትም ሥርዓትም የላቸውም፡፡
- የመናፍቃንን "መዝሙር" ማዳመጥ ከዘፈንም የከፋ ነው፤
- ዘፈን ማዳመጥ ኃጢአት ሲሆን የምግባር ህፀፅ ነው፡፡
- የመናፍቃን "መዝሙር" ማዳመጥ ግን የሃይማኖት ህፀፅ ያለበት በመሆኑ ዓመፅና ክህደት ነው፡፡

፫. ፭ መፍትሔዎች

- ከ፬ አካላት አንጻር እንመለከታለን።

፭. በየደረጃው ያሉ የቤተክርስቲያን ተቋማት

ሀ. ቅዱስ ሲኖዶስ

- ፖሊሲ ማውጣት
- ፖሊሲውን የሚያስፈጽም፣ የሚያግዝ (በሥልጠና፣ በማማከርና በማበረታት)፣ የሚቆጣጠርና ፈቃድ የሚሰጥ ተቋም (ኤዲቶሪያል ቦርድ) ማቋቋም

ለ. ሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ

- ፖሊሲዎችን ማስፈፀም
- ዘማርያንን፣ የሰንበት ት/ቤት ወጣቶችን፣ አሳታሚዎችንና ሌሎች ባለድርሻዎችን /stake holders/ ማወያየት
- ጊዜያዊ መፍትሔ መስጠት
- እርምጃዎችን መውሰድ

ሐ. መንፈሳዊ ኮሌጆች

- ችግሮቹንና መፍትሔዎችን፣ ታሪኩንና ትውፊቱን፣ ... በጥናት ማሳየት
- ሥርዓተ ትምህርት ተቀርጾለት በትምህርት መስክ /Faculty or Department/ እንዲሰጥ ማድረግ

መ. ሰንበት ት/ቤቶች

- ለሰንበት ት/ቤት መዘምራን ሥልጠና መስጠት
- ኦርቶዶክሳዊ መዝሙራትን ብቻ ለየቶ ማስጠናት
- በተለያዩ ጉባኤያት ላይ ሰፊውን የመዘመር ድርሻ መውሰድ
- ኦርቶዶክሳዊ የመዝሙር ካሴቶችን አዘጋጅቶ ማቅረብ (ማሳተም)
- በችግሮቹ ዙሪያ ምእመኑን ማወያየት
- ያፈነገጡ መዝሙራትን አለመዘመርና በጉባኤያቸው ላይ እንዳይዘመሩ በመከልከል
- ከግለሰብ ይልቅ በቡድን የመዘመር ልምድ ማዳበር
- ዘማሪያን የሚወጡት ከነሱ ስለሆነ እነሱን መቅረጽ

፪. የዘማርያን ድርሻ (የዜማና ግጥም ደራሲያንንና አሳታሚዎችን ጨምሮ)

- ራስን በትምህርት ማነጽ፣
- ችግሮችን መለየት፣
- መፍትሔ ማቅረብና መተግበር፣
- ለውይይት ፈቃፈኛ በመሆን ምክክር በማድረግ።

የቀጠለ...

፫. ምእመናን

- ኦርቶዶክሳዊ መዝሙራትን ብቻ መጠቀም፣
- የምናያቸውንም ስህተቶችና ጉድለቶች ማሳየት።

፬. የመዝሙር ማኅበራት

- ከቤተ ክርስቲያን ሕጋዊ እውቅና ማግኘት፣
- ኦርቶዶክሳዊ መዝሙራትን ማዘጋጀትና መዘመር።

ለዛሬ

- ከጽንፈኛ አመለካከት ወጥተን በችግሮቻችን መስማማት፣
- ችግሩን በጥልቀት መረዳትና በቤተክርስቲያናችንና በሀገራችን ላይ የሚያመጣውን ከፍተኛ ቀውስ (Crisis) አርቀን ማሰብ ፣
- በግልጽነትና በቅንነት በመወያየትና በመደማመጥ ከላይ ወደ ጠቆምናቸው መፍትሔዎች ለመሔድ መጣር።

ማጠቃለያ

- መዝሙር ምስጋና&ጸሎት እና ትምሕርት ነው።።
- ሰው ከተፈጠረለት ዓላማ አንዱ ምስጋና በመሆኑ ትክክለኛውን ምስጋና ለእግዚአብሔር ልናቀርብ ይገባል።።
- መዝሙርን በያሬዳዊ ዜማ መዘመር
  - ማንነትን መጠበቅ ነው።።
  - በትክክል ከእግዚአብሔር ጋር የምንገናኝበት ነው።።
  - በቱሪዝም መልክ ለሀገራችን ትልቅ ሃብት ነው።።
- ስለዚህ እያንዳንዳችን ስለ መዝሙር ምንነት ትክክለኛውን ግንዛቤ በመያዝ ለራሳችን እና ለሌሎች ምዕመናን ልናስተምር ይገባል።።

ወሰብሐት ለእግዚአብሔር

ኦሰተያየት...?